# <u>የመደመር ምሥጢር</u>

*በዋሽንግተን ዲሲ፡- የኢትዮጵያ፤የውዪዪትና፤መፍትሔ፤መድረክ (Ethiopian Dialogue Forum) በተደረገው ኮንፈረንስ የመደመርን ጽንሰ ሐሳብ የጥንት ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት እንዴት እንደሚያብራሩት ለመግለጽ የቀረበ።*

ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ
nigatuasteraye@gmail.com

ጳጉሜ ፫ ቀን ፳፻፲ ዓ.ም.
Ethiopian Embassy
Washington, DC

የጥንት ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት <u>"በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ"</u> በማለት ጀምረው በኢትዮጵያ ምድር ላይ ያለውን ኅብረተ-ሰባዊ-ትድምርት <u>በአራት አዕማድ፤</u> <u>በዘጠኝ መራኁተ- ኃይላተ- ቃላት ይተነትኑታል።</u> ከስነ መለኮት እየተንደረደሩ በተጠቀሱት ኃይላተ- ቃላት ህብረተ ሰቡን እያሰናሰሉ በሰርግ ወደ ተመሰረተችው ቤተ ሰብ ይወርዳሉ። የቅኔን ትምህርት በኮፊዳና በውጥንቅጥ ላይ አስጀምረው በሰምና በወርቅ፤ በህብር፤ በሰረዝ በዕሪና ኅብረተ ሰቡን እንድንቃኘው ያስተምሩናል። ለዘመናት ሲደመርና ሲባዛ እስከዚህ ዘመን የደረሰውን የኢትዮጵያን ህብረተ ሰብ እንዴት እንደ ሰሩት ከሀ እስከ ሰ በተዘረዘሩት ለማሳየት እሞክራለሁ።

ሀ.**ደመራ** በስነ መለኮት
ለ.**ደመራ** በስነ አምልኮት
ሐ.**ደመራ** በቅኔ
1. ሰምና ወርቅ
2. ሰረዝ
3. ህብር
4. ዕሪና

መ. **ደመራ** በሰሜኑና በመሀል ኢትዮጵያ
ሠ. **ደመራ** በጉራጌ ህብረተ ሰብ
ረ. **ደመራ** በአርበኛ
ሰ .እንዴት **እንደመር**

## ሀ. <u>ደመራ በስነ መለኮት</u>

# እግዚአብሔር

"ሰበ ንቤ እግዚአብሔር፡- ንብል በእንተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ መለኮት በሥላሴ፡ ወሥላሴ በተዋህዶ" (ሃ አ ም 114፡4 )። በስላሴ አንድነት፤ ባንድነት ሶስትነት እያሉ በስነ መለኮት ይጀምራሉ።

"አንድ አካል ናቸው" ብሎ ክርስቶስ ወደተናገረለት በጋብቻ በሠርግ ወደሚጀመረው ሰባዊ አንድነትና ምንታዌነት ይወርዳሉ። **ህብር** የምትለውን ቃል ከ**ሰብ** ጋራ **<u>ደምረው</u>**ና አዛርፈው የሁሉንም ዕሪና (equilibrium) በመጠበቅ የ**ኢትዮጵያ ኅብረተ ሰብ** በማለት <u>በአራት አእማድ</u> እና <u>በዘጠኝ መራኁት</u> እየተነተኑ ሰርተውታል።

## <u>አራት አእማድ የተባሉት የሚከተሉት ናቸው።</u>

1ኛ፡-**ደመራ** በስነ መለኮት (theology)
2ኛ፡-**ደመራ** በስነ አምልኮ (liturgy)
3ኛ፡-**ደመራ** በታሪክ
4ኛ፡-**ደመራ** በባህል

ከዚህ ባላይ በተዘረዘሩት አዕማድ እየተረዳን በተዘክሮና በአንክሮ ፈጣሪውን ለማምለክ እንጅ፤ በጊዜ በቦታና በሚገጥሙት ክስተቶች የተወሰን ሰባዊ ፍጡራን፤ ወሰንና ገደብ የሌውን ፈጣሪ ፍጹም አውቀነዋል ማለት አይደለም" ይሉና፡- "ዑቅ ወጠይቅ ስርአተ አምሳለ ፍጥረት ዘላዕሌሆሙ በበዘመዶሙ ዘያጸደለድሉ ወያንሰሀስሁ ወዘከመ እፎ ይትቃረቡ በበይናቲሆሙ ወዓዲ ዘከመ እፎ ይትረሀቁ"(ባስል 33፡ 18) ብሎ ባስልዮስ ወደ ተናገረው ይሻገራሉ። ይህም ማለት፡- "አቅምህ በሚፈቅድልህ እየታገዝክ በዙሪያህ ያሉትን የፍጥረታትን መመሳሰል ፡፡ መመጋገብ፤ መደጋገፍ፤ መወራረስ፤ መቃረን፤ መመሳሰል፤ መሳሳብና መገፋፋት ተማር እወቅ " በማለት ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ከ<u>ደመራ</u> ጋራ በተሰናሰሉት **በዘጠኝ መራኁት** የህብረተ ሰቡን ግንኙነት፤ ልዩነት ይሰፍሩባቸዋል፤ ይመዝኑባቸዋል፤ ይመረምሩባቸዋል፤ ይረዱባቸዋል።

## <u>ዘጠኝ መራኁት የተባሉት የሚከተሉት ናቸው</u>

**1ኛ፡-አንድነት፡**- በሶስትነት፤ ሶስትነት በአንድነት
**2ኛ፡-ድማሬ፡**- ደመረ አንድ አደረገ
**3ኛ፡-ኁባሬ ፡- ኀብረ (አኀበረ) ህብር፤ ህብረት፤ ማህበር**
**4ኛ፡-ዕሪና፡- ዐረየ ተካከለ እኩልነት**
**5ኛ፡-ሕድረት፡-** ኀደረ አደረ ሀዳሪ ማህደር
**6ኛ፡-ቱሳሔ፡-** ቶስሀ፡-ጨመረ ቀላቀለ
**7ኛ፡-ሠርግ፡-** ሠርገ፡- ሰርስሮ ገባ።
**8ኛ፡-ቡዓዴ፡-** በዐደ ለየ ባዕድ
**9ኛ፡-ፍልጠት፡-** ፈለጠ፡ ከፈለ ለያየ

በዮዲት፤ በግራኝ፤ በጣሊያን ወረራ፤ በዘመነ መሳፍንት መቃረን፤ በድርቅ ቦታ ለቆ ወደ ሌላ ቦታ መዝመት ፤ በፈቃድ ከቦታ ቦታ በመንቀሳቀስ፤ በመጋባትና በመሳሰሉ ምክንያቶች የኢትዮጵያ ህዝብ በመላ ኢትዮጵያ ከዳር እስከዳር ሲበታተን ሲቀላቀል፤ ሲለያይ ሲደበላልቅ፤ ሲሠራረግ ሲደማመር ሲዋሀድ ኖሯል። በዘመናችንም ቴክኖሎጅ ባስከተለው መቀራረብ ከመቸውም በሰፋና በላቀ ኅብረተ ሰባዊ ደመራ ገዝፏል። ልዩ ልዩ ሀሳብና እምነት ይዘው ወደ ኢትዮጵያ ብዙ ሰዎች ሠርገዋል። የዜ**ግነትን**ና የ**ሰውነትን ትድምርት** መጠን እጅግ ከፍ ብሏል። **ኅብር**ነትም ልቋል።

## ለ. ደመራ በስነ አምልኮት

ስነ አምልኮ (liturgy) በህዝቡ ህሊና ውስጥ ያለውን ጥልቅ ስርጸት ያጠኑ Paul Connerton የተባሉ ሊቅ How Societies Remember (1989) በሚል ርእስ ባሳተሙት መጽሀፋቸው ገጽ 58 ላይ“ በቅርጽና በይዘት ተጽፎ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚሻገረውን ስርአተ አምልኮ በተለያዩ ዘዴዎች ከፋፍሎ ከህዝቡ ባህርይና ስሜት በሚያዛምድ፤ በሚያዋህድና በማይረሳ ተዳሳሽ ምሳሌዎች ማቅረብ ይቻላል” ይላሉ።

Paul Connerton የተናገሩት ከኦርቶዶክስ ተዋህዶ ስነ አምልኮ ግንዛቤ ጋራ ይስማማል። የኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት ሁሉ ተናግረውታል። ከብዙዎቹ አንዱን ጎርጎርዮስ ካልዕ “ወበከመ አስተጋባእካ ለዛቲ ህብስት እንዘ ዝሩት ይእቲ ውስተ አድባር ወአውግር ወታጋቢአ ኮነት አሐተ ጽርስፎራ ህብስተ ፍጽምተ” ጎርጎርዮስ ካልዕ ”ገጽ 373 ቁ 27-28) ብሎ የተናገረውን ለማስረጃ ማቅረብ ይቻላል።

ማለትም፦ “ካንዲት ፍሬ ወደ ብዙ ቅንጣቶች፤ ከብዙ ቅንጣቶች፤ ከቁጥር በላይ ወደ ሆኑ የስንዴ ፍሬዎችና ወደ ቁጥር አልባ ዱቄትነት ይለወጣል። ከዚያም በውሀ በመለወስና በሙቀት በመብሰል ወደ ሕብስትነት በመቀየር ተደምረዋል። በተለያዩ ዓለማት፤ አህጉራት፤ መካናት፤ መንደሮችና ቀበሌዎች የተበተነውን እኛን ደቂቀ አዳምንም፦ በሰላም በፍቅር ለውሰህ ደምረን” በማለት በዓለም የተበተነውን ሰው የሆነውን ሁሉ በ9ኙ መራሁት አምልተን አስፍተን እናይባቸዋለን ።

ባንድምታው አተረጓጎም ስልት፦በዜግነት፤ በመልክአ ምድር፤ በቋንቋ፤ በቆዳ ቀለም ከማይመስሉን በእምነትና በቀኖና ብቻ ከሚመስሉን ከግብጽ ከህንድ ከአርመንና ኮሶርያ ክርስቲያኖች ጋራ **እንደመራለን**። በዜግነት፤ በቋንቋ፤ በመልክአ ምድር፤ በቆዳ ቀለም፤ በሥጋ ዝምድናና በባህል ኢትዮጵያ አንድ ከምታደርገን ጋራ አንድ ነን። ከዚህ ቀጥለን በሰሜን፤ በመሀልና በጉራጌ ህዝብ ታሪክና ባህል ውስጥ የተሰራጨውን የ**ደመራን** ጽንሰ ሀሳብ በቅኔ ትምህርታችን እንመልከት።

## ሐ. **ደመራ** በቅኔ

የቅኔ ትምህርት በኮፊዳና በውጥንቅጥ ይጀምራል። ኮፊዳ ከሰሌን ወይም ከቄጠማ ተሰርታ እየዞርን ከህብረተ ሰቡ የምንለምነውን ምግብ ለመያዝ የምታገለግል ዕቃ ናት። የምንሰበስበው ምግብ ከ**ኮፊዳችን** ገብቶ ሲቀላቀል ህዝባዊና ውስጣዊ ትርጉም ያዘለ ስም አለው። ውሳጣዊ ትርጉሙ፦ **ውጥን ቅጥ** ነው። ማለትም፦ የማይወላውል ቀጥ ያለ ማለት ነው። ወደ ህዝቡ ሲወርድ የተደበላለቀ ማለት ነው።

ውጥንቅጡን ሰብስባ የያዘችው ኮፌዳ በወርቅነት ኢትዮጵያን ትወክላለች። በኮፌዳዋ የተሰበሰበው ውጥንቅጥ በሰምነት በኢትዮጵያ መልክአ ምድር ያለውን ኅብረተ ሰብ ይወክላል። ኮፌዳዋ እንዳትቀደድ እንጠነቀቃለን። ከተቀደደች ቀላቅላና ሰብስባ የያዘችው ውጥንቅጥ ይፈሳል። የኢትዮጵ ዳር ድንበር ከተደፈረም የተደባለቀው ህዝቧ ይበተናል። የቅኔ ትምህርታችንን የምንጀምረው በዚህ ነው። አባቶቻችን እንደነገሩን፤ ከኮፌዳና ከውጥንቅጥ የሚነሳው የቅኔያችን ትምህርት ህብረተ ሰቡን ለመተርጎም ብዙ መራሁት አሉት። ለማመልከት ያህል ጥቂቶችን እጠቅሳለሁ።

1ኛ፡- ሰምና ወርቅ
2ኛ፡-ሰረዝ ሰረዝ  የሚባለውን ማየት ይቻላል።
3ኛ፡-ኅብር
4ኛ ዕሪና፡-አራቱንም ከሰምና ወርቅ ጀምረን ባጭር ባጭሩ እንመለከታቸዋለን።
5ኛ፡-ደመራ በርእሰብሄር፤
6ኛ፡- ደመራ በእንደራሴ፤
7ኛ፡-.ደመራ በምስለኔ

## 1ኛ፡- <u>ሰምና ወርቅ</u>

ሰም በቀላጭነት ባህርዩ ለወርቁ ቅርጽና ይዘት ሰርቶ ይለቃል እንጅ ከወርቁ ጋራ አብሮ አይዘልቆም። በሁለቱ መካከል ዕሪና (equilibrium) ስለሌለ ሰምና ወርቅ ቅኔ የህብረተ ሰብ መግለጫ ሆኖ አያገለግልም። እኔ ወርቅነኝ እያለ የሚቀርብ ሌላውን በሰምነትና በገልነት መንፈስ ተቀጥቃጭና ቀላጭ ማድረጉን አይርሳ። ይህ አነጋገር የዕሪና (equilibrium) አፍራሽ ነው። “ይወደስከ አፈ ነኪር ወአኮ አፈዚአከ” እንዲል፡- በስራህ፤ በግብርህና በባህርይህ ሌላው ወርቅ ይበልህ። አንተ ግን ሰም ልሁንልህ በል እንጅ ወርቅ ነኝ ብለህ አትፎክር።

## 2ኛ <u>ሰረዝ</u>

ሰረዝ የሚባለው የቅኔ ዓይነት ከመደበኛው ሰምና ወርቅ የተለየ፤ ድርብርብ_ወርቆችንና፤ ድርብርብ_ሰሞችን አካቶ የያዘ ነው። ሁሉንም በዕሪና (በእኩልነት) በህብርነት በተመሳሳይ ቅጽል የሚገልጽ በአንድ ብቻ ማሰሪያ ግስ የሚተረጎም ነው። የሰረዝ ቅኔ በይዘቱ ከመደበኛው ሰምና ወርቅ ቅኔ ይሰፋል። ለወርቁ ቦታ የሚለቀው የሰሙ ትርጉምም ይለወጣል። ይህም ማለት ወደ ልዕለ ህሊና በመቀየር እንደ ክርስቶስ እኔ ልውደቅልህ፤ ልሙትልህ፤ ልሰቃይልህ በማለት ለወገን ለአገር ቤዛነትን ያሳያል። በሰጠውና ባሳየው ፍቅር በመወደድና በመከበር ከቀላጭነት ወደ አቅላጭነት ይለወጣል።

ሥጋዬን ይብሉና ደሜን ይጠጡት
ኢትዮጵያ ስትጠፋ ቆሜ ከማያት

እያሉ የሁሉ እናት የሁሉ ሰብሳቢ ለሆነችው ኢትዮጵያ እኔ ልውደቅልሽ እኔ ልሙትልሽ ሰም ልሁንልሽ እየተባባሉ በግንባር ቀደም የሚሰውትን አርበኞችን ይመለከታል።

## መ. <u>ደመራ በሰሜንና በመሀል ኢትዮጵያ ታሪክና ባህል</u>

የታሪኩ ጀማሪ ንግስት እሌኒ ናት። ኢትዮጵያዊት አደለችም። በኢትዮጵያ ምድርም አልጀመረችውም። እሌኒ በዘመኗ ልታገኘው የፈለገችውን ተቀብሮ የነበረውን መስቀሉን አገኘችበት። ራሷ ደመራ ብላም አልሰየመችውም። በያመቱም አላደረገችውም። በአገራችንም እስከ አጼ ልብነ ድንግል ዘመን ድረስ ይታወስ የነበረው እንደ ሌሎች ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት በስንክሳር ንባብ ብቻ ነበር።

በአጼ ልብነ ድንግ ልጅ በአጼ ገላውዴዎስ ዘመን በኢትዮጵያ **ታሪካዊ** አጋጣሚ ተከሰተ። ይህ የተከሰተው ታሪካዊ ክስተት እሌኒ መስቀሉን ፈልጋ ለማግኘት የተጠቀመችበትን ዘዴ (ደመራ) በወቅቱ የነበሩት ሊቃውንት ያጡትን ነጻነት ለማግኘት ተጠቀሙበት።

የግራኝ መሀመድን ተስፋፊነት ለመቋቋም አጼ ልብነ ድንግል በዘመኑ ለነበረው ገናና የፖርቱጋሉ ንጉሥ እርዳታ ጠየቁ። አጼ ልብነ ድንግል ፖርቱጋሎች ከተጠየቁበት ጊዜ እጅግ ዘግይተው ጦርነቱ ከተፈጸመ በኋ በአጼ ገላውዴወስ ዘመን መጡ። መግለጽ የፈለኩት በዘመኑ የነበሩት ካህናት በዘመናቸው የገጠማቸውን ችግር እንዴት እንደፈቱበት ስለሆነ ፖርቱጋሎች ዘግይተው የመጡበትን ምክንያትና ከመጡ በኋላ የፈጸሙትን ስህተት አልፈዋለሁ።

ፖርቱጋሎች በርዳታ ስም ወደ ኢትዮጵያ ከመጡ በኋላ በአድዋና በመቀሌ ሰፈሩ። ከህዝቡ ጋራ ተዋልደውና ተቀላቅለው መኖር ጀመሩ። በቆይታቸው ዘመን ለፖርቱጋል መንግሥታቸው ቅኝ ግዛት ኢትዮጵያን የማዘጋጀት ተንኮል ጀመሩ። በብዛት በሰፈሩባቸው በአድዋና በመቀሌ ህብረተ ሰብ ላይ ተጽእኗቸውን አከበዱት።

ፖርቱጋሎች ተወላጁን ህብረተ ሰብ መናቅና መዝለፍ ጀመሩ። ኢትዮጵያውያንን በሌላው ዓለም እንዳለው ህዝብ ለቅኝ ግዛት የማይጨበጡ፤ በሰውነታቸው ደቃቃወች፤ ለማለት **ቁንጫ** እያሉ ይሰድቧቸው ነበር። ኢትዮጵያውያን ፖርቱጋሎችን ደም መጣጮች ናችሁ ለማለት **ትኋኖች** ይሏቸው ነበር።

ፖርቱጋሎች "መላ ኢትዮጵያን ለፖርቱጋል መንግስት እየገበረ ነው። ከመላ ኢትዮጵያውያን ተለይታችሁ ብቻችሁን ተቀርጣችሁ ቀራችሁ" እያሉ በአድዋና በመቀሌ ያሉትን ኢትዮጵያውያን መስበክ ጀመሩ። ጥቂት ተወላጆችን አሳምነው መንቀሳቀስ ጀመሩ።

ያካባቢው ካህናት በበጎንደር በወሎና በጎጃም ካሉት ካህናት ጋራ በመላላክ "ከመላ ኢትዮጵያውያን ተለይታችሁ ብቻችሁን ተቀርጣችሁ የቀራችሁ እናንተ ብቻ ናችሁ" እያሉ ፖርቱጋሎች የሚሰብኩት ውሸት እንደሆነና፤ በቀረው ኢትዮጵያ ክፍል ለፖርቱጋል መንግስት መገበር ይቅርና ፖርቱጋሎች እንደሌሉና ስለ ፖርቱጋል መንግሥት ቅኝ ገዥነት የሚሰማ ነገር እንደሌለ ተረዱ።

ብሩህ ጭንቅላት ከነበራቸው ሊቃውንቱ አንዱ፤ በመጽሐፈ መሳፍንት ምዕ ፱ ከቁጥር ፳ ላይ የተመዘገበውን፤ "ለትጻዕ እሳት እምቤተ አቤሜሌክ፥ ከመ ትብላእ አብያተ ሴኬም፡ ወትሜሎም:: ወለእመ አኮ እሳት ትጻእ እምቤተ ሴኬም ወትሜሎም ከመ ትብላዕ ቤተ አቤሜሌክ" የሚለውን ንባብ ተመለከቱ ። ይህም ማለት፡-"ከአቤሜሌክ ቤት የተጫሯች እሳት የሴኬምንና የትሜሎምን ቤት ትብላ"

ካህኑ ይህችን ዘዴ እንዴትና መቼ መጠቀም እንደሚችሉ ሲያስቡ፤ ከየቤቱ እየተለኮሰች የምትወጣው የመስቀል ችቦ መብራት ትዝ አለቻቸው። "ከየቤታችን እየተጫረች የምትወጣ የዘንድሮው የመስቀል በዓል እሳት፥ በእርዳታ ስም መጥተው የወረሩንን ፖርቹጋሎችን ቤት ትብላ፥ በዚህ መንገድ በፖርቱጋሎች ላይ የምንወስደው እርምጃ በፈጣሪ ዘንድ ትቀባይነት ሳይኖረው ቀርቶ ረድኤቱን ከነፈገንም በፖርቹጋሎች ሥር ለዘላለም ተጠቅተን ከመኖርና ለልጆቻችንም የተገዥነትን ውርስ ከማውረስ ይሕች ከየቤታችን የጫርናት እሳት እኛኑ ትብላን" በሚል ሀሳብ በመስማማት **ተደምረው** ወሰኑ።

ዘዴውን ፖርቱጋሎች እንዳይሰሙ ተጠንቅቀው ለየደብሩ ካህናት አሰራጩ። በዚያ ሌሊት "ዓኾ ዓኾኋይ ሆይ ሆያዬ ንጎናይ በርሆ" እያሉ የፖርቱጋሎችን ቤት በማቃጠል ፖርቱጋሎችን አጠቋቸው። ከሞት የተረፉት ፖርቱጋሎች በቀይ ባህር በኩል ወደ ሀገራቸው ተመለሱ።

በዚያ ዘመን የመከራቸውን ዘመን ለማሳጠር ብዙ ዘዴዎችን እንደ ተጠቀሙ ይነገራል። ከብዙዎቹ አንዱ በአማረኛ <u>**አሸከት**</u> በትግርኛ <u>**ጸጎጎት**</u> የምትባለውን የመጣበቅ ባሕርይ ያላት ሐርግ ናት። የትግራይ ሰዎች ከእርስ በርሳቸውና ከመላ ኢትዮጵያ ወገናቸው ጋራ ያላቸውን ጥብቅ <u>መደመር</u> ለማሳየት የ<u>መደመር</u>ና የመጣበቅ ባሕርይ ያላትን ይህችን ሐርግ በራሳቸው ላይ በማሰርና እንደመገናኛ ምልክት ተጠቅመውባታል።

ተወልጄ ባደኩበት መንደር በያመቱ በሚከበረው ደመራ በዓል በራስ ላይ እየታሰረች ትታሰባለች። አንዳንድ ሰዎች ለደመራው መታሰቢያ ተደምሮ በሚቃጠለው እንጨት ፍም ላይ ኀዝጉዘው ይቆሙባታል። ለምን እንደሚያደርጉት ሲጠየቁ የሚሰጡት መልስ "<u>ለቁርጥማት መድሀኒት ናት</u>" የሚል ነው።

መምህራን የሚሰጡት መልስ ህዝባውያን ከሚናገሩት ፈጽሞ የተለየ ነው። የመከራው ዘመን ካለፈ በኋላ፤ በመከራው ያለፉ ሰዎች <u>በፈጣሪም ሆነ በሰው የማይቀር ቁጣ ሆኖ</u> ከመጣው መከራ ለመገላገል ለተደረገው **መደመር** መታሰቢያ ነው እንጅ ሀረጓ የምታድነው ቁርጥ መአት የሚባል በሽታ ኖሮ አይደለም ይላሉ።

ለመከራም ለደስታም የህዝብ መገናኛዋ ቤተ ክርስቲያናችን ነበረች። ሀሳብ አቀባባዮችም ካህናትና ነበሩ። በዚህ ምክንያት በኢትዮጵያ ላይ ለጥፋት የሚመጣ አስቀድሞ የሚያጠቃ ህዝባቸውን ለማንቃት ለማደራጀትና ለማገናኘ የሚንቀሳቀሱትን ካህናትንና ምእመናኑን ነው።

"ካህን ሞተ ተብሎ አይነግሩም አዋጅ
እንዲያው በየደብሩ መላክ ነበር እንጅ" ተብሎ ለካህናት ምሾ የተለቀሰላቸው በዚያ ዘመን ነው ይባላል።

በዚህ አጋጣሚ ሳትጠቀስ መታለፍ የሌባት በመከራው ዘመን <u>የአድዋና የመቀሌ ወገኖቻችን ካከናወኗቸው ቅርሶች</u> አንዷ ናት። ይህችም በትግርኛ "ዓኾ ዓኾኋይ ሆይ ሆያዬ ንጎናይ በርሆ" እያሉ በያመቱ በደመራው ዙሪያ የሚያሰሟት ትዝታ ናት። ከሊቃውንቱ እንደሰማሁት የዚህች አረፍተ ነገር ትርጉም፡- "ፖርቱጋሎች መላ ኢትዮጵያ ለፖርቱጋል መንግስት ቅኝ ተገዥነትን ተቀብሎ ሲገብር፤ አንገብርም በማለት ተቆርጣችሁ የቀራችሁ እናንተ ብቻ ናችሁ" ይሏቸው ስለነበረ፤ "እኛ ኢትዮጵያውያን የተቆረጣችሁ እየተባልን በአገራችንና በህዝባችን ስንሰደብና ስንወቀስ አንኖርም፥ ዛሬ በዚህ ችቦ የነጻነት ብርሃን በራልን" እንደ ማለት ነው ብለው ሲናገሩ ሰምቻለሁ።

የትግራይ ሰዎች በመከራው ዘመን ከመላ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻቸው ጋራ የነበራቸውን ጥብቅ አንድነት ለማሳየት፤ የተጠቀመውባታን ጸጎንት ለማስታወስ "**ጽንዒ**" እያሉ መስከረም ፲፯ ላይ እስካሁን በያመቱ ያስታውሷታል። ከላይ እንደተባለ በፈጣሪም ሆነ በሰው የማይቀር ቁጣ ሆኖ ከመጣው መከራ ለመገላገል ለተደረው መደመር መታሰቢያ ለቁርጥ መአት በሽታ ፍቱን መድኃኒት እያሉ እንደሚያስታውሷት ማለት ነው። ከታሪክ ፈልቆ ለዘመናት በተደጋጋሚ በመደረጉ ባህልም ሆኗል።

## ሠ. ደመራ በጉራጌ ኅብረተ ሰብ ታሪክና ባህል

የደመራው ታሪክ በጉራጌ ህብረተ ሰብ ላይም አሻራ ጥሏል። ታሪኩን ባጭሩ እንመልከተው። በተስፋፊነት የዘመተው የግራኝ መሀመድ ሰራዊት ጥቃቱን እጅግ ካበረታባቻው ቦታዎችና ህብረተሰብ አንዱ የጉራጌ ህብረተ ሰብ ነው። በደረሰባቸው ስቃይና መከራ ብዙወቹ ወደ እስልምና ተቀይረዋል። ወደ እስልምና አንቀየርም ያሉት በዘመናችን በሱማሌ ክልልና በሌሎችም ከተፈጸመባቸው መከራና ጭፍጨፋ ያለነሰ ጭፍጨፋ ተፈጽሞባቸዋል። ብዙዎቹ ወደ መህል አገር በመበተን ተርፈዋል። የክርስትና እምነታቸውንም ጠብቀዋል። ይህን ለማስታወስ የጉራጌ ኅብረተ ሰብ በያመቱ ከተበተነበት በ**ደመራ** ዕለት በቤተ ሰብ ይሰባሰባል። ይህም እስካሁን አላቋረጠም።

## ረ. ደመራ በመላ ኢትዮጵያውያን ስሜት የተቀረጸው አርበኛነት

በቅኝ ገዥዎች ለረዥም ዘመን ተይዞ ያልተገዛ ህዝብ ባንድ ወቅት የጀመረውን ነገር ሳይረሳ ስም አጠራሩን በዳህጸ ልሳን እየቀየረ ጠብቆ ለትውልድ ማቀበሉ የታወቀ ነው። ለምሳሌ፡-ከየቤቱ የምንሰበስበውን የትምህርት ቤት ምግብ (ውጥንቅጥ)ኅብረተ ሰብ ድብልቅልቅ እንደሚለው፤ ኢትዮጵያ የሚለውን ጦቢያ፤ ነነዌ የሚለውን ነይነይ እያለ እንደሰየመው ማለት ነው። እንደዚሁ ሁሉ፡-ኅብረተ ሰብ 40ኛ የሚለውን ቁጥር **አርበኛ** ይለዋል።

ያብነት መምህራን ስለአርበኛ ያስተማሩን እንደሚከተለው ነው። አርበኛ ማለት **40ኛ** ለማለት ነው። **ኛ** የምትለው ፊደል ለቁጥርና ለስም ትራስ በመሆን ወደ መግለጫ ቅጽልነት ትቀይራለች። ለምሳሌ፡- ፈረስ በሚለው ላይ **ኛ** ስትደመር ፈረሰኛ፤ በአንድ፤ በሁለት፤ በአስር ቁጥሮች ላይ **ኛ** ትራስ ሆና **ስትደመር** ወደ ገላጭ ቅጽልነት ይለወጣሉ። እንደዚሁም **ኛ** በ **40** ቁጥር ላይ ትራስ ሆና በመደመር 40ኛ በማድረግ ለአገር ለወገን ታዳጊዎች ገላጭ ቅጽል ሆናለች።

የተወሰደችውም ዳዊት "እመሰ በዝሀ ሰማንያ ዓም ወፈድፋዶንሳ እም እላ ጻማ ወህማም" (መዝ 89፡9) ብሎ ከተናገረው አረፍተ ነገር ነው። ይህም "ሰው በሽታ ካላጠቃው ካሰበው ደርሶ መመለስ የሚችለው እስከ **80** ዘመኑ ነው፤ ከዚያ በላይ ግን በእርግና ቋንጃው ይሽማቀቃል። የራሱን ሰውነት መሸከም ይከብደዋል። እንደልቡ ቁልቁለት ወርዶ፤ አቀበት ወጥቶ፤ ዘሎና ሮጦ ሊያደርግ የሚችለው በማእከላዊ ዕድሜው ነው። ማእከላዊ እድሜው የሰማንያ ዘመኑ ግማሽ 40ኛው ናት።

**40**ኛው እድሜ የ**80**ኛ ግማሽ ብቻ አይደለችም። የእሳት ባህርይ ላለው ከ**20** እስከ **40** እድሜክልል እና፤ ከ40 ዕድሜ በላይ 20 ዓመት ደምሮ እስከ **60**ኛ እድሜ ላይ ላለውም ማእከል ነው ይላሉ። **40**ኛ ዕድሜ ላይ ያለ ጎልማሳ ከሱ በታች በ**20**ኛ እድሜ ላይ ያለውንና ከሱ በላይ እስከ **60**ኛ እድሜ ያለውን ዜጋ እየመራ እየደመረ እያስተባበረና እያጣመረ ይዘምታል ይዋጋል ይከላከላል፤ ይነቅላል ይተክላል። ከ**60** በላይ እስከ **80** ዕድሜ ካሉት አዛውንቶች ታሪክ ጥበብ ይማራል። እነሱ በስህተት የሰሩትን ላለመድገም ይማርባቸዋል።**"ከመ ይሚጥ ልበ አበው ሀበ ህሊና ውሉድ ወህሊና ከሀድያን ሀበ ህሊና ጻድቃን"** (ሉቃስ 1፡17)እንዲል፡- ይህም ማለት ያባትቶችን ልብ ወደ ልጆች፤ የከሀዲወችን ልብ ወደ

ጻድቃን ልብ ይመልስ ዘንድ" እንደተላከው እንደ መጥምቁ ዮሀንስ ማለትም ነው። በዚህ ግንዛቤ አርባኛ ማለት፡- እናት አገራችን ኢትዮጵያ በገጠማት በመከራ ዘመን ጸንሳ፤ አርግዛ፤ አምጣ ከየመንደሩ ከየጎሳው ከየቋንቋው የምትወልዳቸው መሆናቸው ነው።

<u>የናታቸው የኢትዮጵያን የጥሪ ድምጽ ሰምተው፤ እየፎከሩና እየሸለሉ ከየመንደሩ ከየጎሳው የሚወጡ እንጅ **40ኛነት** በዘር የሚተላለፍ አይደለም።</u> እነዚህ **40**ኞች ተዋግተው ያሸነፉበትን ድል የተቀዳጁበትን ጦርና ጋሻ፤ የተሸለሙትን ለምድ፤ ቀሚስና ካባ እንደ ሌላው ቆሳቁስ በሥጋ ለወለዷቸው አላወረሱም። <u>እያወረሱ ያለፉት ያ40ኛነት ታሪክና ስሜት ለቀጣይ ትውልድ እንድታስተምርላቸው ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያናቸው ነው።</u> አገር በቀልም ሆነ መጤ ወራሪ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን እየሰደበ፤ እየናቀና እያቀለለ ለብትሩ ዓላማ የሚያደርጋት በዚህ ምክንያት ነው። ይህንን በሚመሰክሩ ካህናትና ምእመናን መከራው ይበረታባቸዋል።

ዶክተር አረጋዊ በርሔ "A Political History of the Tigray people's Liberation Front (1975-1991)" በሚል ርእስ ለDoctoral dissertation ባሳተሙት መጽሐፋቸው ከገጽ 246 እስከ ገጽ 300 ላይ፡-

*"የትግራይ ህዝብ ነጻ አውጭ ግንባር በ1979 አመተ ምህረት አስተሳሰብ ለዋጭ የፕሮፓጋንዳ መርህ ግብር ለሚመለምላቸው ቀሳውስት ዘረጋ። የማሰልጠኑ ዓላማ ቤተ ክርስቲያኗን ከህዝብ ለይቶ በማምታት ስፋቷን ማጥበብና በትግሬአዊነት ላይ ብቻ የተመሰረተ ስሜት በትግራይ ተወላጆች ጭንቅላት መክተት ነው። ቤተ ክርስቲያኗ ለረዥም ዘመናት በህዝቡ አዕምሮ ላይ ስትተቀርጸው የኖረችውን ብሄራዊ የኢትዮጵያነትን ስሜት ከትግራይ ህዝብ አዕምሮ ጠራርጎ በጠባቡ ትግሬአዊነት ስሜት በመተካት የቤተ ክርስቲያኒቱን ይዘት እያጠበቡ ራሷን ቤተ ክርስቲያኒቱን መምታት ነው። የወረዳ ስልጠና የተጀመረው በጠንካራ ትግሉ የታወቀው ካዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በነገረ መለኮት ትምህርት የተመረቀው ገብረ ኪዳን ደስታ ነው። የስልጠናውም ይዘት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ጠቅላላ መዋቅራዊ አስተዳደር በትግራይ ነጻ አውጭ ድርጅት ባለሟሎች መተካትና በቤተ ክርስቲያኒቱ አካባቢ የትግርኛ ቋንቋ እንዲሰፍን ማድረግ ነው"*

ብለው ባሰፈሩት መጽሀፋቸው፤ የወያኔዎችን ማንነት በትዝብት ታሪካዊ ምእራፍ ላይ በማስፈር መጭው ትውልድ ሁሉ እንዳይዘነጋው አድርገዋል። ከዚህ በመቀጠል ጠቅላይ ምንስትር ዶ/ር ዓቢይ አህመድ እ<u>ንደመር</u> እያሉ ይዘው የመጡትን መርሆ እንዴት ተግባራዊ እናድርገው? እያለ ለሚጠይቀው ዜጋ የጥንት አባቶቻች ቢኖሩ ኖሮ ይመልሱት ነበር ብየ የማስበውን ከዚህ በታች አቀርባለሁ።

## ሰ. <u>እንዴት **እንደመር**?</u>

"ወኲሉ ንዋይ ዘይትገበር በእሳት ይነጽህ፤ ወለኲሉ ዘኢይበውእ ውስተ እሳት ለይጥምእዎ ውስተ ማይ። ወያንጽህዎ በማየ አንጽሆ። ወእምድህረ ዝንቱ ይበውኡ ውስተ ትዕይንት" (ዘኍ 31፡22-23) ። ይህም፡-"ከቆሻሻው የሚላቀቀው በእሳት ብቻ ከሆነ በ**እሳት** ይጽዳ፤ በ***ውሀ*** የሚጸዳ ከሆነ በውሀ ይጽዳ። ከዚያ በኋላ ከህዝብ ጋራ ይቀላቀል" ማለት ነው።

መተርጉማን ሊቃውንት እንደሚሉት ***<u>ውሀ</u>*ና *<u>እሳት</u>*** የተጠቀሱበት ምክንያት አላቸው። ***<u>ውሀ</u>*** ሳይዘገይ ስህተቱን ተቀበሎ ይቅርታ የሚጠይቅ ወገን ኅብረተ ሰባዊ ከባድ ቅጣትና ተግሳጽ ሳይጫንበት የይቅርታ ምህረት እንዲያገኝ ያመለክታል። እሳት ደግሞ ስህተቱን ለመቀበል ፈቃደኛ ባልሆነ ወገን ላይ የሚጫንበትን ኅዝባዊ የመጽኛ ሸክም ክብደት ያመለክታል ይላሉ። ይህንን መመሪያ በሚያፈርስ መንገድ ያለንስሀና ያለጸጸት ያለ ይቅርታ መደመር ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል። ስነ አምልኮታችን "እመቦ ዘወድቀ በውስተ ኃጢአት ኢይርሳ እስመ ዘኢይትረሳእ" እያለ ብርቱ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል። (.ቅ ከገጽ 125 እስከ ገጽ 126) እያለ ያስገነዝባል። <u>ይህም፡- "ከህዝብ ወገን ህዝባዊ ስህተትና በደል ፈጽሞ በህዝብ እየተከሰሰና እየተወቀሰ ከሆነ እንደተራ ነገር አይርሳ። በቂም በበቀል ተገፋፍቶ እንደ ጎዳኝ ልጉዳው ብሎ</u>

ርምጃ መውሰድን የሚከለክለውን ያህል በጸጸት በንስሀ ሳይጸዳ **መደመርንም** ኦርቶዶክሳዊ እምነት በጥብቅ ይከለክላል።

ሆኖም አዕምሯችን እንዲመዘግብ እንጅ እንዲረሳ ሆኖ አልተፈጠረም። የሚረሳ ጭንቅላት ያላት አህያ ብቻ ናት። በተፈጥሮ በመርሳቷም ቅድስት አያደርጋትም። በደረሰበት ጭንቅ ታፍኖና ተወጥሮ በመጃጀት (alzheimer) በሽታ የአዕምሮው ቋት ተጠቅቶ ቢረሳና ቢዘነጋ ቅዱስ አይባልም። ይህማ ከሆነ ሃላፍያትን እንደማያስታውሱ እንስሳት መሆን ነው።

የሚያስመሰግንና ብጹዕ የሚያሰኘውም መበቀል ሲቻል፤ የብቀላን ስሜት ማሸነፍ መቻል ነው። የምንረሳውማ ከሆነ ምን ያስደንቃል? ምኑን ተውነው? በሰውናትችን በዜግነታችንና በኢትዮጵያዊነታችን ትድምርታችን የሚሰረዝ አይደለም። የማንደመረው ከሚያሻግርብን ክፉ ባህርዩ ፤ ግብሩ ሽፍጡ ራስን ለመከላከል ነው።

የፈጸመውንና በመፈጸም ላይ ያለው ክፉ ተግባሩን እያወቅን በዘመድ በጥቅም ተታለን በመደመር እንዳንተባበረው "ምልሁ እምውስቴታ ኢየሀሉ ተኩላ ምስለ  በግዕ አንቄ ምስለ ርግብ ክርዳድ ምስለ ሥርናይ" (ቅ አ ገ 216 ቁ 11)።  እያለ ስነ አምልኳችን ያስጠነቅቀናል። ይህም ማለት፡- "ተኩላ ከበግ፤ ጭልፊት ከርግብ፤ ስንዴ ከእንክርዳ ጋራ እንዳይቀላቀል ተጠንቀቃችሁ ለዩ"።

"ዕቀብ ኩልነ ዘእንበለ ጻእብ፤ወዘእንበለ ተመውዖ፤ ወዘእንበለ ማዕቀፍ።አድኅነ አእጋሪነ እምዳህጽ፤ ወአዕይቲነ እም አንብእ፤ ወነፍስተነ እሞተ ኃጢአት። ወደምረነ ምስለ እለ ይድህኑ ብከ በጸሎተ ኩሎሙ እለአስመሩከ" (ሊጦን ዘሰርክ)። ይህም ማለት፡- "ያለ ጻብ፤ ያለ መሸነፍ፤ ያለ እንቅፋት፤ እግሮቻችንን ከዳጥ፤ አይኖቻችንን ከእንባ፤ ነፍስና ሥጋችንን በሰው ህሊና ትዝብት ውስጥ ገብተን ተመዝነን ቀለን ከመገኘት ጠብቀን። ከነዚህ ነገሮች በንስሀ ከተላቀቁ  ወገኖች ጋራ ደምረን የሚለውን እየደገምን እንድንጸልይ ሊጦን የተባለው መጽሐፍ ያስገነዝበናል።

በመጨረሻም ስነ አምልኮታችን "አድህነነ  እምተደምሮ በዕልዎት ወርኩስ ምስለ አላውያን ወአረማውያን" (ቅ 102 ቁ 86) በማለት፡- "በክህደትና በሽፍጥ ህሊናቸው ከረከሰባቸው ከሀዲወችና ጨካኞች ጋራ ከመደመር አድነን"። ብሎ ይደመድማል።

ተመልካች ሆይ የ**መደመርን** መርሆ ይዘው የመጡት የዘመናችን መሪ ጠቅላይ ምኒስተር ዶ/ር ዓቢይ አህመድ "ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ውጭ ኢትዮጵያ የለችም" ያሉት ምን አሰገድዷቸው ይሆን?

ከጠቅላይ ምንስተር ዶ/ር ዓቢይ እንማር። ከቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን እንደኛ በጥምቀት ባይወለዱም፤ ታሪክ፤ ባህልና ዜግነት ከኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያናችን ጋራ ስለደሚደምሯቸው "የደመራውንና የጥምቀቱን በዓል አታበላሹብን" እየሉ በተቀደሰ ድፍረት ሲመጡ ከመደመር በቀር "ምን አገባህ" ሊል የሚደፍር የለም።

በኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ያላችሁ ኢትዮጵያውያን ገኖቼ ሆይ ! እኛ ካህናት ስንከፋፈል እናንተም የእኛን መከፋፈል እንደምሳሌ በመውሰድ መከፋፈላችሁን አቁሙ !  ስህተት ተከታይ ላለመሆም የቤ ክርስቲያናችሁን እምነትና ቀኖና እያነበባችሁ ቤተ ክርስቲያናችሁ ተረዷት እወቋት። ሰው ላለማስቀየም፤ ወይም ወዳጅን ለመደገፍ ወይም እለታዊ ጥቅም ላለማጣት እውነቱን ባንደበታቸው እየመሰከሩ፤ ከሀላፊነት ለመሸሽ ካህኑ እያለ እኔ ምናገባኝ ማለት የበለጠ በደል ነው።

የኦርቶዶክስ ተዋህዶ የክርስትና እምነት በታሪክና በባህል በመሸፈኑ ወደ ሌላ ድርጅት ሄድን የምትሉ ከኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ውጭ ያላችሁም፤ ከላይ በተገለጸው መንገድ እምነቱ ታሪኩ ባህሉ መያዙ ጠቀመ እንጅ አልጎዳም። የጎዳው ትውልዱ ይህን አለማወቁ ነው።

አባቶቻችሁ ኢትዮጵያዊነት ጠብቀው ያወረሱን ከላይ በተገለጸው ታሪክና ባህል መሆኑን አትርሱ። አባቶቻችሁ ከዚህች ቤተ ክርስቲያን ያልተለዩት ክፍተቱ የሚያስከትለውን ጉዳት በማጤን እንጅ ካህናቱን የሚንቁበትና የሚጸየፉበት ጉድለት ሳያዩ ቀርተው አይደለም። በዚህ ዘመን በተፈጠርኩት እኔን በመሳሰልን ቀሳውስት ድካምና ውሱኑነት እየተቀየማችሁ በዚህች ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በጥምቀት <u>መደመራችሁን</u> የቀነሳችሁ ወገኖች ! በነፍስም ሆነ በሥጋ ከሚገጥመን ፍርድ መዳን የምንችለው በፈጣሪ ምህረት ብቻ ነው። ድርጅት በመቀየር አይደለም።

ከ27 የመከራ ዘመን በኋላ በዚህ ዓመት በኢትዮጵያ አገራችን ታሪክ እየተደገመ ነው። የመደመሩን መንፈስ አማራው ከጎንደር፤ ኦሮሞው ከሸዋና ሌላው ሁሉ ዜጋ ከበርሀ ከጫካ ከያለበት አስተጋብቶታል፤ ነገር ግን ክቡር ለማ መገርሳ **“ኢትዮጵያ ሱስ ናት”** እያሉ፤ ዶ/ ር ዓቢይ እ**ንደመር** እያሉ የመደመር ጠላት ከሆነው ጉያ ሰንጥቀው ወጥተው **ሲደመሩ** ታሪክ ተደገመ። ፖርቱጋሎች እንዳደረጉት ወያኔዎች ለ27 ዓመት ባሳደሩበት ተጽእኖ አብኛው የትግራይ ህዝብ ከ<u>መደመር</u> በመዘግየቱ ገና ፍጹም አልሆነም።

በዚያ ዘመን በትግራይ ምድር የነበሩ አባቶቻችን ያደረጉትን ዛሬም የዚህ ዘመን መከራ የጠራችሁ አርበኞች ወገኖቻችን ድገሙት። በዚያ ዘመን በመቀሌና በአድዋ የነበሩ ወገኖቻችን ፓርቱጋሎችን ደም መጣጮች **ትኋኖች** ናችሁ ውጡልን ብለው ከመካከላቸው ማስወጧቸውና በፖርቱጋሎች ተንቀውና ተጠቅተው **ቁንጫ** ይባሉ የነበሩትን ማስገባታቸውን ትውልድ እንዳይረሳ በያመቱ <u>**”ትኋን ውጭ ቁንጫ ግቢ**</u>“ እያሉ ከ**ደመራ** በዓል ጋራ አያይዘው ማስታወሳቸውን አትርሱ። ዛሬም የፖርቱጋሎች መንፈስ ያላቸውን ከመካከላችሁ አስወጡ ! እንደመር በማለታቸው እንደ እነ አቶ ገብረ መድኅን አርአያ ያሉትን ወገኖችን ጋብዙ፤ እቀፉ። አስገቡ !

ፖርቱጋሎች በፈጠሩት የመከራ ዘመን የትግራይ አባቶቻችን ከመላ ህብረተ ሰብ ጋራ የነበራቸውን <u>መደመር</u> ለማሳየት የተጠቅሙባታን አሸክት (ጸጎጎት) መስከረም <u>፲፰</u> ቀን **ጽንዒ** እያሉ እስካሁን በያመቱ ያስታውሷታል። እናንተም ዘንድሮ በተግባር ትደግሙት ዘንድ ታሪክ እየጠራችሁ ነው።

እኛ ኢትዮጵያውያን የተቆረጣችሁ እየተባልን በአገራችንና በኅብረተ ሰባችን ስንወቀስ አንኖርም ብለው የቀደሙ አባቶቻችን “ዓኾ ዓኾኋይ ሆይ ሆያዬ ንጎናይ በርሆ” እያሉ የፖርቱጋሎችን ሰንሰለት በጣጥሰው ከኢትዮጵያ ወገናቸው ጋራ በመደመር የመከራውን ዘመን አሳጥረዋል። ዛሬም በዚህ ዘመን ያላችሁ የትግራይ ተወላጆች ወገኖቻችን! ከመላ ኢትዮጵያ ሊቆርጣችሁ በመሞከር ላይ ካለው ገንጣይ ሰንሰለት በጥሳችሁ በመውጣት ከመላው ኅብረተ ሰባችሁ ጋራ በ<u>**መደመር**</u> ታሪካችሁን እንድትደግሙ መላው ኢትዮጵያዊ ወገናችሁ በናፍቆት እየጠበቃችሁ ነው።

አሁን በደረስንበት በደስታና በመርዶ <u>ድምር</u> የዚህን ዓመት <u>***ደመራ***</u> እንድናስታውሰው የፈቀደ አምላክ፤ ደስታችንን ፍጹም እንዲያደርግል በጸሎት የታጀበውን ተግባራችንን ይባረክልን።